# የተባበሩት መንግስታት የሶማሊያና ኤርትራ ተቆጣጣሪ ቡድን ሪፖርትና የኤርትራ መንግስት ቅጥፈት

የኤርትራ ባለስላጣናት አሁንም የቅጥፈትና የመንሸራተት ፖሊሲያቸው አጠናክረው ቀጥለውበታል፡፡ በሐምሌ ወር የተባበበሩት መንግስታት ድርጅት የሶማሊያና ኤርትራ ተቆጣጣሪ ቡድን ኤርትራን አስመልክቶ ያወጣውን ሪፖርት በማስመልከት ከአንድ ሳምንት በፊት በተባበሩት መንግስታት የአርትራ ቋሚ መልዕክተኛ የሆኑት አምባሳደር አርኣያ ደስታ ከቪኦኤ ጋር ያደረጉትን ቃለ ምልልስና የሪፖርቱን እውነታ በማነጻጸር ማየት ያስፈልጋል፡፡ ተቆጣጣሪ ቡድኑ የኤርትራ መንግስት አሁንም የአፍሪካ ቀንድን በማተራመስ እና የተባበሩት መንግስታት ሪዞሉሽን 1844 (2008) በግላጭ እየጣሰ እንደሆነ፣ በሶማሊያ ፀረ-ፌዴራል መንግስት የሚንቀሳቀሱ የጦር አበጋዞች እና የአልሸባብ አመራሮች ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር ዘርፈ ብዙ ድጋፍ በማድረግ የሶማሊያን ብሎም የአከባቢውን ሰላም በማወክ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ እንደሆነ ቡድኑ በማያሻማ አኳኋን አረጋግጧል፡፡

የኤርትራ መንግስት በኤርትራ ውስጥ ያለውን የሰብኣዊ መብት ጥሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያባበሰው ከመሆኑ ባሻገር በየመንና በተለያዩ ጎረቤት አገሮች በመንቀሳቀስ አልሸባብን በመደገፍና የጅቡቲ እና ኢትዮጵያ ተቃዋሚዎችን በመርዳት የተጠለበትን ማዕቀብ ችላ በማለት የአካባቢው ሰላም እንዲደፈርስ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ እና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሳንክሽን ኮሚቴ በኤርትራ መንግሰት ላይ ተጨማሪ እርምጃ እንዲወስድ ተጠይቋል፡፡ የአምባሳደር አርኣያ ደስታ ቅጥፈት ግን በሚገርም ሁኔታ ሰላም ወዳድ እና ትሁት በመምሰል በኤርትራና ጅቡቲ መካከል ምንም ችግር እንደሌለ፣ የኤርትራ መንግስት ከአልሸባብም ሆነ ከጦር አበጋዞች ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለው ጭልጽ አድርገው መካዳቸው የሚያስደምም ነው፡፡ ለነገሩ ማነኛውም የኤርትራ መንግስት ባለስልጣን እውነት ለመናገር አልታደለም ይሆናል፡፡ አምባሳደሩ እንደሚሉት ከሆነ እንደውም አንዳንድ የጸጥታ ምክር ቤት አባላት ኤርትራ ላይ የተጣለውን ማዕቀብ ትክክል ስላልሆነ ሊነሳ ይገባል የሚሉ አሉ ይላሉ፡፡ የኤርትራ ልዩ ልኡክ አምባሳደር አርኣያ ለተባበሩት በመንግስታት ድርጅት ማዕቀብ ኮሚቴ ባቀረቡት ሪፖርት እንደሚያሳየው የኤርትራ መንግስት ከአልሸባብ ጋር የነበረውን ታሪካዊ ግንኙነት በመተው ድጋፉን ለሶማሊያ ፌደራል መንግስት እየሰጠ ይገኛል ማለታቸው ከዚህ በፊት ከአልሸባብም ሆነ ከሌሎች የጦር አበጋዞች ምንም አይነት ግንኙነት የለንም ብለው ከደው ይከራከሩበት የነበረውን በራሳቸው አንደበት ከአልሸባብ ጋር ግንኙነት እንደነበራቸው ማመናቸውን ያሳያል፡፡

የኤርትራ መንግስት የሚንሸራተተው ሚስኪኑ የኤርትራን ህዝብ ለማሳመን ከሆነ የሚሆን አይመስለኝም ምክኒያቱም ህዝቡ የሃያ ሁለት ዓመታት የኤርትራ መንግስት ቅጥፈት እና ተርምስ ምን ዓይነት ዋጋ እያስከፈለው እንደሆነ በተግባር ጠንቅቆ ያቃል፡፡ ግን የትኛው አገር ነው ብለው ቢጠየቁ መልስ እንደማይኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ አምባሳደር አርኣያ የተቆጣጣሪ ቡድኑ ሪፖርት መሰረተ ቢስነው ማለታቸው አዲስ ባይሆንም ቻይና፣ ሩስያ፣ ፓኪስታን እና ጣሊያን ተቃውሞታል በማለት ድቤ ሲመቱ ሰምተናል፡፡ በእርግጥ እነዚህ አገሮችም ሆነ ሌሎች በመጀመሪያ አከባቢ መውጣት የለበትም ብለው እንደነበር የሚታወቅ ቢሆንም ዋና ቁም ነግር የሚሆነው ግን በምን ምክኒያት ነው የተቃወሙት የሚለውን ማየቱ ነው ትክክል የሚሆነው፡፡ አምባሳደር አርኣያ እንደሚሉት የኤርትራ መንግስት ልክ እንደ አብራሃም በግ ደግ እና የዋህ ስለ ሆነ እነዚህ

አገራት አዝነውለት ሪፖርቱ ኤርትራን አይመለከትም የሚል እንድምታ እንዳለው ለማስመሰል እንደ ቀጠፉት ሳይሆን ከየራሳቸው ቀጥታዊና ተዘዋዋሪ ጥቅም አኳያ ተነስተው እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አገራት ለምን ሪፖርቱን እንደተቃወሙት አንድ በአንድ መተንተን ባያስፈልግም ለዚህ ንባብ ሲባል በጥቂቱ ማየቱ ተገቢ ይሆናል። የዚህ ጽሑፍ አንባቢ እንደሚረዳው ቻይና በታሪኳ ማዕቀብ ደግፋ እንደማታቅ የሚታወቅ ሆኖ አብስቴን አደረገች ማለት ግን በግላጭ ደግፋለች ማለት እንደሆነ፣ በኤርትራ የተጣሉትን ሁለት ተከታታይ ማዕቀቦች ደግሞ ቻይና በድምጸ- ተአቅቦ ድጋፏን እንደሰጠችበት በቀላሉ የምንረዳው ይመስለኛል። ሩስያ በሚመለከት ደግሞ ከምዕራባዊያን ጋር ያላትን የቆየ ቅራኔ በመነሳት አንዳንድ ጊዜ የፍሪካ ቀንድ ጉዳይ የአሜሪካና አውሮፓ አጀንዳ አድርጋ የማየትና የተዛባ አመለካከት በመያዝ እንደምትቃወም እና በተለይ በአፍሪካ ቀንድ ያለውን ጂኦ-ፖለቲካዊ ተጽእኖ ላይ ለመቆናጠጥ ስለምትፈልግ፣ በኢትዮጵያና ኤርትራ ያለውን ግጭት ለመሸምገልና ለማስታረቅ ካላት ፍላጎት እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ያም ሆነ ይህ ዘግይተውም ቢሆን የአከባቢውን ሰላም ለማናጋት እየተንቀሳቀሱ እንደሆነና ለኤርትራ ህዝብም እንደማይጠቅም በመረዳታቸው ሪፖርቱ ይፋ እንዲሆን ተደርጓል። እውነታው ይህ እያለ አምባሳደሩ ግን የአለም ማ/ሰብ ይታዘበኛል ሳይሉ የኤርትራ መንግስት የቅጥፈት ስትራቴጂ ሲያራምዱ ተስተውሏል።

ሪፖርቱ የኤርትራ መንግስት ውስጣዊ ሁኔታ ሲገመግም እንዳስቀመጠው በአንድ በኩል የፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቅ ቁልፍ የድህንነት እና ወታደራዊ ታማኞች ቡድን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝቡ፣ ወታደራዊ አፈሻሎች በተለይ ደግሞ ወታደራዊ ኮማንደሮችና ሚኒስትሮች መካከል ተከፋፍሎ እንደሚገኝ፣ አቶ አሊ አብዱን ጨምሮ የአየር ሀይል አባላት፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የጦር አባላት ኩብለላ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፋ መልኩ አገሩ ጥሎ ወደ ተለያዩ ጎረቤት አገሮች እየወጣ የሚገኝ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ (Exodus) የኤርትራ ወስጣዊ ሁኔታ በምን ዓይነት አሳሳቢ ሁኔታ እንደሚገኝ ያሳያል ። የዚህ እውነታ መገለጫ የሚሆነው በጃኒዋሪ 21/2013 <<**የፎርቶ ፍጻሜ**>> እየተባለ የሚታወቀው በእነ ኮለኔል ኦስማን ሳልህ የሚመራ የከሸፈ የህዝብ ብሶት ሙከራ ከላይ የተጠቀሰው መሰነጣጠቅና መከፋፈል ያሳያል። የኤርትራ መንግስት በአፍሪካ ቀንድ የማተራመስ ፖሊሲውን በሶማሊያ ኬኒያ የመን እና ደቡብ ሱዳን በድህንነት አባላቱ አማካኝነት በጦር መሳሪያ፣ ኮንትሮባንድ፣ የገንዘብ ዝውውር (Money-laundering) እና በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ተሰማርቶ እንሚገኝ ሪፖርቱ ያመለክታል። በተለይ ደግሞ የኤርትራ የጦር መኮንኖች በህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር በገዛ ዜጎቻቸው በሱዳን፣ ግብጽ ሳይናይ በረሃ ለሚገኙት ህገ ወጥ አዘዋዋሪዎች ለራሻይዳና በደዊን ሽፍቶች እየሸጡ ልክየለሽ ዶላር እንዲከፍሉ አሊያም ለአስገድዶ መድፈር፣ አሰቃቂ ድብደባና ግድያ እንዲዳረጉ በማድረግ የድረሱልኝ ጭሆት ለቤተሰቦቻቸው እንዲያሰሙ በማድረግ እስከ አርባሺ ዶላር እንዲከፍሉ ያስገድዳሉ። የሚሰበሰበውን ገንዘብ ደግሞ በስዊዝ ባንክ በኤርትራ ዲፕሎማት የባንክ ሂሳብ እንደሚቀመጥ በሪፖርቱ ተረጋግጧል፡

የኤርትራ መንግስት የሶማሊያ ፖለቲካዊ ውስጣዊ ሁኔታ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ በመፍጠር የሶማሊያ የሰላም ጥረት እያደናቀፈ እንደሆነ ተቆጣጣሪ ቡድኑ አረጋግጧል። በአህመድ አብዲ ሀሺ (**Hashara**) አማካኝነት የሶማሊያ ፌዴራል መንግስትን የሚዋጉ እንደነ ህመድ ኑር እና አብዲ ዋል የመሳሰሉት የአልሸባብ አመራሮች በኤርትራ መንግስት ፔሮል እንደሚከፈላቸውና ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ ከኤርትራ የሚቀበሉ እንደነበር፣ ይህ የሚከናውነው ደግሞ የኬኒያ መንግስት ከአገሩ ያባረራቸው በኬኒያ የኤርትራ አምባሳደር የነበሩ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ለሱዳን እና ኢራን የኤረትራ አምባሳደር ሆነው እያገለገሉ የሚገኙ የቀድመው የኤርትራ መንግስት የድህንነት አመራርና የብርጌድ 72 አመራር የነበሩ መሀመድ ማንታይ

አማካኝነት እንደሆነ ሪፖርቱ አረጋግጧል፡፡ አብዲ ዋል ኖቬምበር 1/2012 የሶማሊያ አለማቀፍ ኤርፖርት በሮኬት ሲናጥ፣ በሶማሊያ የአፍሪካ ህብረት ሚሽን በእሳት ሲጋይ ዋና ተዋናይ የነበረ አሸባሪ መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ታዲያ አምባሳደሩ ተባብረን እንሰራለን የሚሉት ከእነዚህ አሸባሪዎች እያለ ማንን ለማደናገር ነው ለሶማሊያ መንግስት ዕውቅና ሰጥተናል ተባብረንም እሰራን ነው ብለው የሚዋሹት?

የኤርትራ መንግስት  በቅጥፈት እጅ ከፍንጅ ሲያዝ ቶሎ ብሎ የመንሸራተት እና እግር የመላስ ልማዳዊ ድርጊቱ  ማየት ዋነኛ መለያ ብህሪው በመሆኑ ይመስለኛል በነሀሴ መጀመሪያ አከባቢ እኚህ አምባሳደር ራሳቸው ኤርትራ ለሶማሊያ መንግስት እውቅና ትሰጣለች ተባብራም ትሰራለች የሚል የልመና ብጤ የሚመስል  ሪፖርቱ ከሚያደርስባቸው ግርፋት ለማመለጥ ሲባል ያደረጉት ንግገር እንደሆነ ለመገመቱ አያዳግትም፡፡ ምክኒያቱም በአንድ በኩል የኤርተራ መንግስት አሁን በሶማሊያ ያለው በህዝብ የተመረጠ መንግስት የሶማሊያውያን መንግስት አይደለም ብሎ ባለ በሌለ አቅሙ የአልቃይዳ  ክንፍ የሆነውን አልሸባብ እና ፈደራል መንግስቱን ለመጣል የሚንቀሳቀሱ የጦር አበጋዞችን  በግልጽ እየደገፈ ፣በሌላ በኩል ደግሞ ዕውቅና ሰጥቻለሁ ማለት ይጣረሳል፡፡ ስለሆነም  የኤርትራ መንግስት ሁሌ ትንፋሽ ሲያጥረው  የሚፈጽመው ቅጥፈትና ማጭበርበር እንጂ ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት አንድም ቀን አስቦት እንደማያቅ ይታወቃል፡፡ የኤርትራ መንግስት የተባበሩት መንግስታት የጸጥታ ምክር ቤት ሪዚሉሽን 1907 በስውር በመጣስ የጦር መሳሪዎችንና መለዋወጫ ዕቃዎች (**Spare parts**) በግብርና ሚኒስቴሩ  አማካኝነት የተጣለበትን ክልከላ ጥሶ ወደ ኤርትራ ሲያስገባ እንደቆየ በሪፖርቱ ተረጋግጧል፡፡

በተጨማሪ የተባበሩት መንግስታት ተቆጣጣሪ ቡድን የኤርትራ መንግስት የተባበሩት መንግስታት የጸጥታ ምክር ቤት ሪዞሉሽን 2023 በመጣስ ከማዕድን፣ ከዲየስፖራ የሚሰበስበውን 2% ታክስ እና በውጭ አገራት በተለያዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች ሚሰበስበውን ገንዘብ ለወታደራዊ አላማ እና የአከባቢውን ሰላም ለማወክ እያዋለው እንደሆነ ቡድኑ አክሎ ገልጻል፡፡ በመሆኑም የኤርትራ መንግስት የሚያራምደው የቅጥፈትና የዜሮ ድምር ፖለቲካዊ አካሄድ ማንንም ሊያታልል እንደማይችል አምባሳደር አርአያ ሊገባቸው ይገባል፡፡ ቸር እንሰንብት!

**ልኡል ዮሐንስ**